# «የኢትዮጵያ ተስፋ»

መክብብ ማሞ

ከጥቂት ወራት በፊት ፕሮፌሰር መስፍንና አቶ አስራት በሰሜን አሜሪካ የአንድነት ፓርቲ የድጋፍ ማኅበራትን በጎበኙ ጊዜ ከፕሮፌሰር መስፍን ጋር ፊትለፊት ተገናኝቼ የመነጋገር ዕድል ገጥሞኝ ነበር። አዛውንቱ ምሁር በንግግራቸው ነገር ማብዛት የማይወዱና በአንክሮ የሚያዳምጡ ናቸው። በበርካታ ጉዳዮች ላይ ጥልቅና በልምድ የዳበረ አመለካከታቸውን በተጋራሁበት ጊዜ በንግግራችን መሃል ውስብስብ የሆነውን የኢትዮጵያ ጉዳይ በተመለከተ መልስ ያላገኘሁለትን አንድ ጥያቄ አቀረብኩላቸው። «ከእንግዲህ ወዲህ የኢትዮጵያ ተስፋ ምንድነው?» የሚል። ጥቂት በማሰብ አቀረቀሩና ሲጋራቸውን አንድ ጊዜ ሳብ አድርገው ቀና ብለው አዩኝና «አንተ ነሃ!» አሉኝ። ያልተጠበቀው መልስ በመካከላችን ጸጥታን አሰፈነ።

የብርቱካን ዘመነኛ ነኝ - የብርቱካን ትውልድ። ይህ ትውልድ አዲስ ነው። ከቀደምት ሥርዓቶች ወይም የፖለቲካ አመለካከቶች በምንም መልኩ ያልተበረዘ ትውልድ። እንዲያውም እነኚሁ የፖለቲካ አመለካከቶች ያመጡትንና እስካሁን መፍትሔ ያልተገኘለት የኢትዮጵያ ችግር ገፈት ቀማሽ ትውልድ። የቴዲ አፍሮ ትውልድም ነው። «አንድነትን ፣ ፍቅርን ፣ መተባበርን ፣ . . . » የሚሰብክና ሥር ለሰደደው የኢትዮጵያም ችግር መፍትሔ ይኸው እንደሆነ አበክሮ የሚያምን ትውልድ። «የኢትዮጵያ ተስፋ»!!

ወዲ ዜናዊ ይህንን ትውልድ ጠንቅቆ ያውቀዋል። ቢችል የራሱ ማድረግ ይፈልጋል። ካልቻለ ደግሞ ጥላቻው ከፍቀሩ የበለጠ ስለሆነ ለማጥፋት ይፈልጋል። የብርቱካን ትውልድ የወዲ ዜናዊን «የረጅም ጊዜ ዕቅድ» ተግባራዊ እንዳይሆን የሚያደርግ ትውልድ ነው። የሕዝብን አመለካከት ለመለወጥ ታጥቆ የተነሳ ትውልድ ነው። በሕግ የበላይነት የሚያምንና ስለሃቅ የቆመ ትውልድ ነው። ከችግሩ ይልቅ መፍትሔው ላይ የሚያተኩር ፤ «አንድነት ፣ አንዱና ብቸኛው አማራጭ ነው» የሚል ትውልድ ነው። ወዲ ዜናዊ ግን የዚህን ትውልድ ሙዚቃና የፖለቲካ ስብከት መስማት አቃተው ፣ አንገፈገፈው ፣ መቀመጫ ነሳው ፣ እንቅልፍ አሳጣው ፣ ጉልበቱን ብርክ አስያዘው። አሰበ . . . «መፍትሔ አገኘለት» - እስር ቤትም ከተተው። «የኢትዮጵያን ተስፋ» ዘብጥያ ጣለው። ከረቸመው። . . . ግና «ተስፋን» ማሰር ይቻል ይሆን?

የሽምግልና ሥርዓት ድንቅ የሆነ ኢትዮጵያዊ ተቋም ነው። ሽማግሌዎች የማይታረቅ በሚመስል ቅራኔ ውስጥ ያሉትን ወገኖች በማነጋገር ብሎም በማስማማት

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ቅራኔን ወደ ዕርቅ በመቀየር የሚተጉ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ታላቁ መጽሐፍ «የሚያስታርቁ ብፁኣን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና» የሚል የክብር ማዕረግ ለሽማግሌዎች የሰጠው፡፡ ማስታረቅ ፣ መሸምገል ደግሞ የሁሉም ሃይማኖቶች መሠረታዊ እምነት እንደሆነ ለመረዳት ጥልቅ የሃይማኖት ምርምር የሚያሻው ጉዳይ አይደለም፡፡ ለዚህም ነው የቀድሞ የቅንጅት አመራሮችን ከእስር ለማስፈታት በተደረገው ሽምግልና ውስጥ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፣ የእስልምና ፣ የፕሮቴስታንት ፣ የካቶሊክ ፣ ወዘተ እምነት ተከታዮች የሆኑ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉት፡፡ ታዲያ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእነዚህ ሰዎች የድፍረትና የሃቅ ቃል ይጠብቃል፡፡ «የኢትዮጵያን ተስፋ» ለጊዜያዊ ጥቅም ብለው አሳልፈው ይሰጣሉ ብዬ አላስብም፡፡ ሃቅን በመሻር የሽምግልናን ተቋም አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር ይፈጽማሉ ብዬም አልገምትም፡፡ እውነትን ፊት ለፊት በመናገር ከታላቁ አምላክ የተሰጣቸውን «የልጅነት» ማዕረግ እንደገና ይሸለሙታል ብሎ ትውልድ ተስፋውን ጥሎባቸዋል፡፡ ሆኖም እስካሁን በርካታ ቀናት አልፈዋል - ዝምታውም ያስፈራል፡፡ ሕዝብ የሽማግሌዎችን መልስ እየጠበቀ ነው - ትውልድም እየቃተተ፡፡ እናንተ ሽማግሌዎች «የኢትዮጵያ ተስፋ» መልሳችሁን እየጠበቀ ነው፡፡

ከዚህ የሽማግሌዎች መልስ መስጠት ጋር በተያያዘ መልኩ በአሁኑ ጊዜ በብዙዎች ዘንድ «ከእንግዲህ ወዲህ ምንድነው መደረግ ያለበት?» የሚል ጥያቄ ከሁሉም አቅጣጫ ሲሰነዘር ይሰማል፡፡ ከዚህ በፊት እንደተለመደው በየኤምባሲው እና በየአገራቱ ውጭጉዳይ መስሪያቤት ደጃፍ ጩኸትና መፈክር ለማሰማት ማሰቡ በወዲ ዜናዊና ግብረአበሮቹ ደጋግሞ ለመሞኘት ከመፈለግ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም፡፡

ታዲያ ምን ይደረግ?

ይህ ጥያቄ ከወራት በፊት በቀድሞው የፓኪስታን መሪ ሙሻረፍ ለእስር ተዳርገው የነበሩትን የጠቅላይ ፍርድቤት ዳኛ ኢፍትካር ቻውድሪ እንዲፈቱ የሙያ ባልደረቦቻቸው የሥራ ማቆም አድማ በማድረግ እና ከሕዝቡ ጋር በመተባበር ያደረጉትን ንቅናቄ ያስታውሰኛል፡፡ ተቃዋሚ ሰልፈኞቹ የዳኛውን መፈታት ብቻ ሳይሆን የጠየቁት በተደጋጋሚ ያሰሙ የነበረው አንድ መሪ መፈክር ነበር - "Go, Musharraf, go!" የሚል፡፡ ይህ ንቅናቄ በራሱ ደግሞ ባለፈው የታላቁ ሩጫ ጊዜ ሕዝባችን ለወዲ ዜናዊ የፈከረውን አስታወሰኝ - «**አትጨማለቅ ሥልጣኑን ልቀቅ**»!! የሚለውን፡፡

mekbma@yahoo.com

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com